“ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከወኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።” ማቴ.ምዕ3ቁ16-17

## ምስጢረ ጥምቀት

በማኅፀን እያለ ሲዘል እንደንቦሳ
ዛሬ ነው ያወቅነው እጅ እንደሚነሳ
መጥምቁ ዮሐንስ ጌታውን ሲያወሳ።
የጌታን መንገድ አዘጋጁ እያለ
ጉዞውን ወደ በረሀ በደሰታ ቀጠለ።
በዛ ምድረ በዳ ምንም በሌለበት
አንበጣና ማርን ምግብ ባደረገበት
የዓለምን ኑሮ ንቆ በሄደበት
ለካስ አምላክ ኖሯል መንገድ የሆነለት
ጽድቅን ለመፈጸም በምስጢረ ጥምቀት።
መጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ዙሪያ
ለብዙ ነፍሳት መዳን በር ሆኗል መግቢያ።
የንስሐን ጥሪ ጩኸት እያሰማ
ጥምቀትና ንስሐን በአንድ ላይ አስማማ።
ወልድ በትህትና ሲጠመቅ በዮሐንስ
ታዩ እኮ ተራሮች ሲዘሉ እንደፈረስ
ምድር ስትናወጥ ከዳር እዳር ድረስ
ኮረብቶች ዝቅ ሲሉ ዮርዳኖስም ሲሸሽ።
እንዴት ያስደንቃል የጥምቀቱ ምስጢር
የምወደው ልጄ እያለ አብ ሲናገር
መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ
በራሱ ላይ ሲሰፍር
ኢየሱስ ተጠምቆ ሲሆነን ምስክር
ከዚህ የበለጠ ምንም የለም ተአምር
ለእኛ የአዳም ልጆች መዳኛ በምድር
መንግስቱን መውረሻ ሰማያዊውን ክብር
ዲያብሎስን መጣያ መንፈሳዊ በትር።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
(ለንደን14/12/06)